# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 88 ጥር 13 2002 ዓ.ም


**ምርጫን እንደመሰለያ መሳሪያ የሚጠቀመው ወያኔ በድህረ ምርጫ 97 በህዝባችን ላይ የፈጸመው አይነት ፋሽስታዊ ጭፍጨፋ እንዳይደገም ከተፈለገ ነጻ እና ገለልተኛ የሆነ የምርጫ አስፈጻሚ አካላት፤ ለሁሉም እኩል የሚያገለግል የሚዲያ አገልግሎት፤ ታማኝነታቸው ለህገመንግሥቱ ብቻ የሆነና ከፖለቲካ ወገናዊነት የጸዱ የፖሊስ፤ የመከላኪያና የደህንነት ተቋማት መመስረት ይኖርበታል።**

**ለወያኔ እድሜ መራዘሚያ ህጋዊና ሞራላዊ መሰረት እንዲያስገኝ ታስቦ በሚካሄድ ምርጫ መሳተፍ ለህዝባችን የሚያስገኘው ፋይዳ አይኖርም!!!**

## ወያኔ በጥምቀት በአል አከባበር ወቅት በርካታ ሰራዊቱን አሰማርቶ እንደነበር ተዘገበ

የአዲስ አበባው ወኪላችን ከትናንት በስቲያ የተከበረውን የጥምቀት በአል ምክንያት በማድረግ እንደዘገበው፣ ሲቪልና ዩኒፎርም ልብሶችን የለበሱ የወያኔ የጸጥታ ሀይሎች ቁጥር ከመቼውም ጊዜ በላይ በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሮ ታይቷል። በጋዜጠኛው ግምት ከ10 ሺ በላይ ወታደራዊ ዩኒፎርም የለበሱ የመከላከያ፣ የፌደራልና የአዲስ አበባ ፖሊስ ሰራዊት አባላት በየጉራንጉሩ ተመድበው የክትትል ስራ ሲሰሩ ነበር። ይህ አሀዝ የሲቪል ልብስ የለበሱ የወያኔ የደህንነት አበላትን ቁጥር እንደማይጨምርም አስታውቋል። ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ወታደሮችን በማሰለፍ ከህዝቡ በኩል ሊነሳ ይችላል ብሎ የፈራውን ተቃውሞ ለማፈን ዝግጅቱን አጠናቆ እንደነበር ሪፖርተራችን ዘግቧል። በቡድን በመሆን ይጨፍሩ የነበሩ ወጣቶች የፌደራል ፖሊሶችና የመከላከያ ሰራዊት አባላት በአንድነት ቆመው ጥበቃ ወደሚያደርጉበት አካባቢ ሲደርሱ “ዝም፣ ዝም” እያሉ ይናገሩ እንደነበር ሪፖርተራችን አያይዞ ገልጿል።

በአገሪቱ ውስጥ የሚታየው ውስጣዊ ተቃውሞ የሚያስጨንቀው ወያኔ፣ የሰራዊቱን ቁጥር በየጊዜው በማብዛትና የክትትል ስራዎችን በመስራት ማፈን ይችላል ብሎ እንደሚያምን ይታወቃል። አሁን ያለው ከ400 ሺ በላይ ሰራዊት አልበቃው ብሎ በቅርቡ ወታደሮችን ለመመልመል ማስታወቂያ ማውጣቱም ይታወሳል። በድምበሮች አካባቢ የሚታዩ አለመግባባቶች፣ የተለያዩ ታቃዋሚዎች በወያኔ ላይ የሀይል እርምጃ ለመውሰድ የሚያደርጉት ዝግጅት፣ በትግል ላይ ያሉ የአንዳንድ የተቃዋሚ ሀይሎች እየተጠናከሩ መምጣት እንዲሁም በአገር ውስጥ በተለይም ከእነ ጄኔራል ተፈራ ማሞ እስር ጋር ተያይዞ በአማራው ክልል እየታየ የመጣው እንቅስቃሴ ወያኔን ለተጨማሪ ሰራዊት ምልመላ እንዳነሳሳው ምንጮቻችን ተናግረዋል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በሎንደን የሚገኙ ኢትዮጵያውያን የሱዳንንና የወያኔን ድርጊት አጥብቀው አወገዙ

በእንግሊዝ አገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያን፣ በሎንደን ከተማ፣ በኢትዮጵያ ተራድዖ ማኅበር አዳራሽ ጥር ፱ ቀን ፪ሺ፪ ዓ ም በተደረገው ኅዝባዊ ስብሰባ፣ በወያኔ/ኢሕአዴግና በሱዳን መሀል፣ አሳሪነት በሌለው የቅኝ ገዢዎች መረጃ ላይ ተመርኵዞ የተደረሰውን ውል የአገርን ሉዓላዊነት የሚሸራርፍ በመሆኑ እናወግዘዋለን ማለታቸውን ከወንድሙ መኮንን ዘገባ ለመረዳት ተችሎአል።

ዘጋቢው እንደገለጸው አካባቢውን በድንብ የሚያውቁት፣ ጎንደርን በምክትል አስተዳዳሪነት የመሩት ሊቀ መምራን አበባው ይግዛው፣ ስለ አካባቢው ውበት፣ ልማት፣ በሚጣፍጥና በሚገባ አማርኛ ጥርት አድርገው አስረድተዋል። ሊቀመምህራን አበባው እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ለምን እንዲህ ዓይነቱን የአገር ክህደት ወንጀልን መቋቋም እንዳለበት ሲያስረዱ፡ “ድንበሩ የተጣሰበት፣ ሰላም የለውም፣ ድንበር የሌለው ዜጋ እንቅልፍ የለውም፣ ድንበር የሌለው አገር ስለልማትና ዕድገት ሊያወራ አይችልም” ማለታቸውን ወንድሙ መኮንን ዘግቦአል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ኢትዮጵያውያን ለዲሞክራሲ የሚያደርጉት ትግል ፍሬ እንደሚያፈራ ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ ገለጹ

የግንቦት 7 ሊቀመንበር የሆኑት ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ በአሜሪካን አገር ታዋቂ ለሆነው ደብለው ቢአር ኢ ለተባለው የቴሌቪዥን ጣቢያ በሰጡት ቃለምልልስ ላይ፣ በኢትዮጵያ ያለው የዲሞክራሲ ትግል በመጨረሻ ፍሬ ማፍራቱ የማይቀር ቢሆንም፣ ምእራባዊያን ከዲሞክራሲ ሀይሎች ጎን የሚቆሙ ከሆነ ዲሞክራሲን ለማምጣት የሚደረገው ትግል ረጅም ጊዜ አይወስድም ሲሉ ተናግረዋል ።

“ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ ሞት የተፈረደባቸው ሰው አይመስሉም” ሲል ዘገባውን የጀመረው ጋዜጠኛ ጀረሚይ ዲቤል፣ ዶ/ሩ “በአጠቃላይ በኢትዮጵያ የሚታየው የፍርድ ሂደት ድራማ ነው። በትክክለኛ አረዳዱ ካየነውም በኢትዮጵያ ውስጥ የህግ ስርአት የሚባል ነገር የለም።” ሲሉ መናገራቸውን ዘግቧል።

ዶ/ር ብርሀኑ “የወያኔ መሪዎች በምእራብ አገሮች የሚሸጠውን የፖለቲካ ሸቀጥ በደምብ የሚያውቁ መሰሪ ሰዎች ናቸው” ካሉ በሁዋላ፣ ወያኔ ሽብርተኝነትን እዋጋለሁ የሚለው በአገር ውስጥ ለፈጸመው የዘር ጭፍጨፋና የሰብአዊ መብቶች ረገጣ ሽፋን እንዲሆነው በማሰብ መሆኑን በአጽንኦት ተናግረዋል። ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የወያኔ የግድያ ሀይሎች እርስበርሳቸው መታኮሳቸው አገዛዙ ምን ያክል በፍርሀት ውስጥ ተሸብቦ እንደሚገኝ ያሳያል ተባለ

ሰሞኑን በአዲስ አበባ ከተማ በወያኔ የግድያ ሀይሎች መካከል የተከሰተው የተኩስ ልውውጥ አገዛዙ በከፍተኛ ፍርሀት እና መረበሽ ውስጥ እንደሚገኝ የሚያመላክት መሆኑን የግንቦት 7 አመራር አባል የሆኑት አቶ ሙሉነህ ኢዩኤል ተናገሩ። አቶ ሙሉነህ ለግንቦት7 ራዲዮ በሰጡት አጭር ቃለ ምልልስ እንዳስታወቁት ወያኔ ላለፉት 20 ዓመታት ያለአግባብ የተቆጣጠረውን ሥልጣን ለሌላ ተጨማሪ 20 እና 30 ዓመታት ለማራዘም በሚከተለው የአፈና ፖሊሲ፡ ተቀናቃኝ መስሎ የሚታየውን ሁሉ በፍርሃት ለማንበርከክ ለጸጥታ ሃይሉ “የምትጠረጥሩትን ሁሉ ተኩሳችሁ ግደሉ” እስከማለት የሚደርስ ትዕዛዝ እንዳስተላለፈ ይህ ደግሞ አገዛዙ ወደ ማይቀርለት የፍጻሜው ውድቀት እያመራ መሆኑን ከማሳየትም አልፎ በተለይ በአሁኑ ሰዓት ከጠመንጃ ውጭ የሚተማመንበት ምንም ሌላ ሀይል እንደሌለው የሚያሳይ ነው ብለዋል።

አቶ ሙሉነህ አያይዘውም፣ የወያኔ ወታደሮችና ፖሊሶች ባገኙት ሰዎች ላይ መተኮስ መጀመራቸው የወያኔ ባለሚሎች እንደ ገደል ማሚቶ እየተቀባበሉ የሚያስተጋቡት ህገመንግሥት ተብዬ ነገር የተጻፈበትን ወረቀት ዋጋ ያህል እንኳ ፋይዳ የሌለው መሆኑን እራሱ ወያኔ በተደጋጋሚ ከሚፈጽማቸው የአደባባይ ወንጀሎች ማየት ይቻላል ብለዋል ።

ሰሞኑን ሪፖርተር በተባለው ጋዜጣ ላይ “በአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን የቦሌ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ የክትትልና ኦፕሬሽን ክፍል ሰራተኞች ጥር 4 ቀን 2002 ዓም በስራ ላይ እንዳሉ ገርጂ አካባቢ ከሚገኘው የፌደራል ፖሊስ ካምፕ በፖሊሶች በተተኮሰ ጥይት ከፍተኛ የመቁሰል አደጋ” ደረሶባቸዋል የሚል ዜና መውጣቱ ይታወሳል። ተኩሱ የተፈጸመው በፌደራል ፖሊስ አባላት ካምፕ በር አከባቢ ሲሆን፣ በተኩሱ ጉዳት የደረሰባቸው ደግሞ ሲቪል የለበሱ የክትትል ሰራተኞች ናቸው እንደሪፖርተር መረጃ ምንጭ። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ወያኔ የአባይ ውሀ ባለቤትነት ለግብጽ እንዲሰጥ አልተስማማሁም ሲል ለማስተባበል ሞከረ፣ ባለሙያዎች ግን ወያኔ እያምታታ ነው እያሉ ነው

ሰሞኑን የአባይን የባለቤትነት መብት ለግብጽ መንግስት አሳልፎ በመስጠቱ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ከፍተኛ ቁጣ መቀስቀሱን ተከትሎ፣ የወያኔው የውጭ ጉዳይ መስሪያቤት ለማስተባበል ሞክሯል። የወያኔው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መስሪያቤት በድህረገጹ ባስተላለፈው መረጃ ፣ በግብጹ አልሀራም ጋዜጣ የተዘገበው አብዛኛው መረጃ እውነት ቢሆንም፣ ኢትዮጵያ የግብጽን የአባይ ባለቤትነት ተቀብላለች የሚለው መረጃ ግን ሀሰት ነው ብሎአል። ምንም እንኳ ወያኔ ጉዳዩን ለማስተባባል እየሞከረ ቢሆንም የፖለቲካ ተንታኞች ግን ወያኔ እያምታታ መሆኑን ጠቁመዋል።

አንድ ስማቸው እንዳይገለጽ የፈለጉ የውሀ ፖለቲካ ባለሙያ ፣ የአልሀራም ጋዜጣ ዘገባ እውነትነትን የሚያሳዩ ነጥቦች መኖራቸውን ገልጸዋል። ባለሙያው እንደሚሉት “በመጀመሪያ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤቱ መልስ የሰጠው ጋዜጣው ጉዳዩን ካነሳውና የኢትዮጵያውያንን ቁጣ ከቀሰቀሰ በሁዋላ ነው። ወያኔ በሱዳን በኩል ያለውን መሬት አሳልፎ የሰጠው እንዲሁ በድብቅ በመደራደር ነው። አሁን ከግብጽ ጋር የተደረገውም ስምምነት ይህንኑ ነገር የሚያመለክት ነው። ስለዚህ ወያኔ ጉዳዩን በድብቅ ለመያዝ መፈለጉ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በወያኔው ውስጥ ያለው የስልጣን ሽኩቻ እንደቀጠለ ነው

የአዲስ አበባው ወኪላችን እንደዘገበው፣ መለስ ዜናዊ መጪውን ምርጫ ሰበብ አድርጎ ሊያራግፋቸው የሚፈልጋቸው ሰዎች ተቃውሞዎችን እያቀረቡ ነው። ዘጋቢአችን የውስጥ ምንጮችን ዋቢ አድርጎ እንደዘገበው አንዳንድ የመባረር ፍንጭ የተሰጣቸው ባለስልጣናት፣ “ለ19 አመታት ከህዝቡ ጋር ደም ከተቃባንና በውጭም በውስጥም ለመኖር በማንችልበት ሁኔታ ውስጥ ከወደቅን በሁዋላ አሁን በስልጣን ሽግሽግ ስም ስልጣን ልቀቁ መባላችን ተገቢ አይደለም ሲሉ ፣ ለፈላጭ ቆራጩ አምባገነኑ ገዢ መለስ ዜናዊ አቤቱታ አቅርበዋል። ባለስልጣናቱ አክለውም ጊዢው ፓርቲ ከስልጣን የሚያነሳን ከሆነ፣ በፓርላማው የጸደቁት ጥቅሞች ብቻ በቂ ስለማይሆኑ ተጨማሪ የአገልግሎት ካሳና ሌሎች ጥቅማጥቅሞችም ይስጠን ሲሉ ጠይቀዋል።

መለስ ዜናዊ በጤና ምክንያት ከ 2020 በላይ በስልጣን ላይ እንደማይቆይ እየተናገረ ሲሆን፣ ከአስር አመት በሁዋላም ስልጣኑን ለልጁ ወይም ለባለቤቱ ይሰጣል ተብሎ ይጠበቃል። የመለስ ዜናዊ ህልም ምን ያክል የሚሳካ ይመስልዎታል ለተባሉት አንድ የግንቦት 7 አባል ሲናገሩ፣ መለስ ዜናዊ እንደሚያልመው እስከ 2020 የሚቆይ ከሆነና ስልጣኑንም ለልጁ ለማስረከብ የሚያስብ ከሆነ፣ ድክመቱ ያለው በሰውየው ሳይሆን በእኛ ላይ ይሆናል ማለት ነው።” ብለዋል።

## ወያኔ በሕዝባችን ላይ በዘራው ፍርሃት ላይ በጋራ መዝመት ያለብን ዛሬ ነው!

የወያኔ መሪዎች በዘወትር ፍርሃትና ሽብር መወጠራቸው ገሃድ ነው። አስቀድሞ ህሊና ሳይኖራቸው የህሊና ሰላም ሊኖራቸው አይችልምም ነበር። በየእለቱ በደል እያደረሱበት ያለው ሕዝብ አፀፋ ለመመለስ የሚያስችለውን አጋጣሚ ማስመለጥ አይፈቅድ ይሆናል ብለው መስጋታቸውም የሚጠበቅ ነው። የመለስና ግብረ አበሮቹ በፍርሃት ቆፈን መያዝ የሥራቸውና የባህሪያቸው ውጤት ነውና አይደንቀንም። መለስ እንደተሸሸገ አዲስ አበባን በሙሉ ዓይኑ ሳያይ ሃያ ዓመት ሊሞላው መሆኑ ከማስገረም ያለፈ ፋይዳ የሌለው ጉዳይ ነው ። እኛን እጅግ የሚያሳሰበን ጉዳይ ግን ወያኔ የራሱን ፍርሃት ወደ ሕዝብ እያጋባ የመሆኑ ሃቅ ነው።

የፈሪ ዱላ ክፉ ነው፤ አይንና አፍንጫን አይለይም። የወያኔም የፈሪ ዱላ አቅመ ደካማውን ከጎበዙ፤ ሕፃኑን ነፈስ ካወቀው አይለይም። ለምሳሌ አግዓዚ የተባለው የወያኔ ቅልብ ጦር በማን ላይ ለምን እንደሚተኩስ የማያውቅ ፈጽሞ የታወረ ተቋም ነው። የፌደራል ፓሊስም ከፓሊስነት ይልቅ የአግዓዚነት ባህርዩ ያመዝናል። ሰሞኑን በአዲስ አበባ ገርጂ እንደታየው ፌደራል ፓሊስ ሲደናበር በከተማ ፓሊስ አባላትም ላይ ሳይቀር ይተኩሳል።

በርካታ ኢትዮጵያዊያን ፍርሃት በፈጠረው የወያኔ ጨካኝነትና ድድብና ተጠቅተዋል። በዚህም ምክንያት ከጥቂት ዓመታት በፊት በወያኔ ፍርሃት ይስቅ ከነበረው ሕዝብ ውስጥ ጥቂት የማይባለው ክፍል ዛሬ ከራሱ ከወያኔ ባላነሰ በፍርሃት ቆፈን ተይዟል። ይህ በእጅጉ ያሳስበናል።

ከዚህም በተጨማሪ የወያኔ ፍርሃት የእርስ በርስ ስለላን ማለትም "ጆሮ ጠቢነትና" ወሬ አቀባይነት ተሰምቶ ወደ ማይታወቅበት ደረጃ አሳድጎታል። ይህ የእርስ በርስ መሰላሰል በሕብረተሰባችን ውስጥ የነበረውን እና ለዘላቂ አብሮነታችን እጅግ አስፈላጊ የሆነውን ማኅበራዊ መተማመንን እያጠፋው ነው። አንዳንዶች የሚያወሩት ነገር ሲያጡ ፈጥረው ማሳበቅንም እየተማሩ ነው። ወያኔ ጓደኝነት፣ አብሮ አደግነትና ጉርብትና የሚያስጠቁ ነገሮች እንዲሆኑ እያደረጋቸው ነው። ይህ እጅግ አሳሳቢና አፋጣኝ መፍትሄ የሚሻ ጉዳይ ነው።

በሕዝብ ውስጥ ፍርሃትን በመንዛት ወያኔ ጉልበተኛ መስሎ ለመታየት የሚያደርገው ጥረት ግንባር ቀደም ተጠቃሚው የስለላ ተቋሙ ነው። የወያኔ የስለላ ተቋም ደካማ ነው። በዘር የተሰባሰቡ ማይማን የረቀቀ እውቀት የሚጠይቅ የስለላን ተግባር የማከናወን አቅም የላቸውም። በዚህም ምክንያት ነው "የስለላቸው" መነሻና መድረሻ አሉባልታና ወሬ ብቻ የሆነው። ስለዚህም ነው አፍንጫቸው ሥር የሚደረገውን እንኳን ማየት የማይችሉ ሆነ ሳለ አንዳች ነገር ድንገት እጃቸው ውስጥ ከወደቀ በብዙ የፈጠራ ታሪኮች የሚያጅቡት። የወያኔ ሰላዮች የተካኑበት ሥራ ቢኖር ራሳቸው ያጠመዱትን ፈንጂ በቪዲዮ እየተቀረጹ ማምከንን ነው። የወያኔ ሰላዮች ደካማነታቸውን በጭካኔ በማካካስ በሕዝባችን ውስጥ የነዙት ፍርሃት የሌላቸውን ጉልበት እየሰጣቸው ነው።

ወያኔ ሕዝብን በማስፈራራት የራሱን ፈሪነት ለመደበቅ ይሞክራል። በእጁ ውስጥ የገቡትን እስረኞችን ሳይቀር በራሳቸው ላይ እንዲመሰክሩና ስለ ወያኔ አይበገሬነት እንዲደሰኩሩ እያደረገ ነው። ይህ ደግሞ የእስረኞችንና ቤተሰቦቻቸውን ብቻ ሳይሆን የሰፊ ማኅበረሰብን ስሜት በእጅግ የሚጎዳ በመሆኑ የአፀፋ እርምጃውም የዚያኑ ያህል የመረረ ሊሆን ይችላል።

ፍርሃትን ማንገስ የተለመደ የአምባገነኖች የመጨቆኛ መሣሪያ ነው። ፍርሃት ለተወሰነ ጊዜ ዜጎች ተዋርደው፣ ተረግጠውና ተቀጥቅጠው እንዲገዙ የማድረግ አቅም አለው። ሆኖም ግን ፍርሃት ያቆመው ሥርዓት ለመናድ ጊዜ አይፈጅበትም። ፍርሃት ያቆመው የበርሊን ግንብ በሰዓታት ውስጥ መፈራረሱ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። በአገራችንም ቢሆን በፍርሃት ለመግዛት ሞክረው ለጥቂት ዓመታት የተሳካላቸው አምባገነኖች ሁሉ አስከፊ ውድቀትን ወድቀዋል። የወያኔም ውድቀት ተመሳሳይ እንደሚሆን ጥርጥር የለንም።

በየእለቱ እየጠነከረበት ያለው የፍርሃት በሽታ ወያኔን አጠቃላይ ቀውስ ውስጥ ሊያስገባው እንደሚችል መገመት ይቻላል። ይህ ከመሆኑ በፊት ግን እንደ ሕዝብ የሚደርስብን ማኅበራዊ ጉዳት ከፍተኛ ሊሆን ይችላል። በራስ መተማመን የጎደለው ማኅበረሰብ ችግሮቹን ፈትቶ ወደፊት ለመራመድ ያለው አቅም በእጅጉ የተወሰነ ነው።

በዚህ ሁሉ ምክንያት በፍርሃት ላይ መዝመት የሚኖርብን ዛሬ ነው። በፍርሃት ምክንያት ወዳጅን አሳልፎ ለወያኔ መስጠት በፈጣሪም፣ በእውነትም፣ በሕዝብም በታሪክም የተነቀፈ አስፀያፊ ተግባር ነው። ከአሁን በኋላ ይህንን መታገስ ፈጽሞ የለብንም። አውቀውም ሆነ ሳያውቁ ራሳቸውን በወያኔ የድርጅት፣ የስለላ ወይም የመጨቆኛ ተቋም ውስጥ ያገኙ ወገኖቻቸን ሰልፋቸውን ፍትህና ነፃነትን ከተጠማው ሕዝብ ጋር በማድረግ የወያኔን ተቋም ለወያኔ ማጥፊያነት ካላዋሉት በስተቀር ከተጠያቂነት የማያመልጡ መሆኑን ልናሳውቃቸው እንወዳለን።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ**

### በሎንደን የሚገኙ ኢትዮጵያውያን . . . ከገጽ 1 የዞረ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሰቲ የታሪክ ምሩቅ የሆኑት አቶ አገኘሁ ገበያውም ጥልቅ የሆነ ጥናታዊ ጽሁፍ ማቅረባቸውን ከዘገባው ለመረዳት ተችሎአል።

በውይይቱ ላይ የተገኙ ኢትዮጵያውያንም "ባለ ጉዳዩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይወያይበት፣ ከጀርባው በምስጢር፣ ወያኔ/ኢሕዴግና የሱዳን መንግሥት የተስማሙበት የድንበር ውል፣ አገራዊ ክህደት ሲሆን፣ ልክ ከዚህ በፊት እንደተደረገው የአገሪቷን ሉአላዊነት የሚሸራርፍና የኢትዮጵያን አንጡራ መሬት ለሱዳን አሳልፎ የሚሰጥ ደባ መሆኑን በመገንዘብ፣ ድርጊቱን እናወግዘዋለን" ብለዋል። ተሰብሳቢዎቹ በአቋም መግለጫቸው ላይ " የኢትዮጵያው አምባገነን ገዢ፣ ከሕህባችን ጀርባ፣ በምስጢር ከሱዳን መንግሥት ጋር ሲደራደር፣ ከሱዳን መንግሥት በኩል ብቻ አንዳንድ የራሳቸውን የደስታ መግለጫዎች ሲያወጡ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን በወያኔ መንግስት በኩል ምንም መረጃ እንዳያገኝ የተደረገበትን ደባ፤ የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት በድንበራችን አካባቢ ያለውን ሰፊ መሬት ለሱዳን በድብቅ አሳልፎ ሲሰጥ፣ ለስሙ የሕዝብ ተወካዮች ናቸው በሚባሉት በምክር ቤቱ/ፓርላማ የገጠገጣቸው ሰዎች እንኳን ሳያውቁ ክሕደት ፈጽሟልና፣ በራሱ ሕገ መንግሥት ሳይቀር ውክልና እንደሌለው ያረጋገጠ በመሆኑ በጥብቅ ሊወገዝ ይገባዋል" ይላሉ

ተሰብሳቢዎቹ አያይዘውም "ወያኔ/ኢሕአዴግ የሕዝብ ውክልና ሳይኖረው ባለጉዳዩን ሕዝብ ሳያማክር በጉልበት አስገደዶ፣ ኗሪውን ከቀዬው ፈንቅሎ፣ ከሱዳን መንግሥት ጋር የፈጸመውን ውል ወደፊትም እንደ ሕጋዊ ድርድር ቆጥረን ልናከበረው እንደማንችል፣ ለአፍሪካ ሕብረት፣ ለሱዳን መንግሥትና ለዓለም ሕብረተሰብ ከውዲሁ ልናስታውቅ እንወዳለን" ማለታቸው ተገልጿል። "ቤታቸውን፣ ንብረታቸውን፣ እርሻቸውን፣ ድንበራቸውን ላለማስደፈር ሲፋለሙ ከተጎዱት የአካባቢው ኗሪ ወገኖቻችን ጎን አብረን በመቆም፣ በአሁኑ ሰዓት መብታቸውን ለማስከበር የሚጠቀሙበትን ማንኛውንም እርምጃ በመደገፍ እንተባበራለን" የሚሉት ኢትዮጵያውያኑ፣ በመጨረሻም "ወያኔ/ኢህአዴግ በኢትዮጵያ ላይ የፈጸመውን ደባ በአንድነት በማውገዝ ፣ አደጋውንም ለመከላከል አብረን መታገል ይኖርብናል" ሲሉ ለተቃዋሚ ፓርቲዎችና ለሲቪክ ማህበራት ጥሪ አቅርበዋል ።

### ወያኔ የአባይ ውሀ ባለቤትነት ለግብጽ . . . ከገጽ 1 የዞረ

በራሱ አንድ ነገር እንዳለ ያመለክታል። በሌላ በኩል ደግሞ አልሀራም የጠቀሳቸው መረጃዎች አብዛኞቹ እውነት መሆናቸውን ወያኔ ራሱ አምኖአል። ይህ ማለት መረጃዎቹ በስብሰባው ከተሳተፉት ሰዎች መካከል ካልተሰጠ በስተቀር አልሀራም ከየትም ሊያገኘው አይችልም። በተለይም ኢትዮጵያና ግብጽ ያላቸው ዲፐሎማሲያዊ ችግር እየታወቀ ባለበት ጊዜ አንድ ትልቅ ጉዳይ ካልተፈጸመ በስተቀር በጠቅላይ ሚኒስትር ደረጃ ስምምነት አትፈራረምም። ጉዳዩ ንግድ ቢሆን ኑሮ የንግድ ሚኒስተሩ ብቻቸውን መሄድ ይችሉ ነበር። ጠቅላይ ሚኒስተሩ ግን ወደ አዲስ አበባ የሄዱት የውሀ ኤክስፐርቶቻቸውን ጭምር ይዘው ነው። ይህ አንድ ስምመነት ለመኖሩ የሚያመላክት ነው ብለዋል።

ባለሙያው አያይዘውም "ግብጽ የኢትዮጵያን እድገት እንደማትፈልግ እየታወቀ፣ ግዝፍ የሆነ ኢንዱስትሪዎችን በኢትዮጵያ ለመትከል ተስማምታለች። ለዚህ ማሳያው በአባይ ላይ ወይም ለሌሎች ፕሮጀክቶች ማሰሪያ ከአለማቀፍ ተቋማት ብድር ሲጠየቅ ዘወትር የምታደናቅፈው ግብጽ ናት። አሁን በድንገት በኢትዮጵያ ግዙፍ ፋብሪካዎችን አቃቁማለሁ ማለቷ በመልሱ አንድ ነገር ማግኘቷን ያሳያል። ያ ባይሆን ኖሮ ግብጽ ፋብሪካዋን በአገሩዋ አቋቁማ ስራ አጥ ዜጎቿን ስራ ትቀጥርበት ነበር። ብለዋል።

በግብጽ ባለሀብቶች ይገነባል የተባለው የኤሌክትሪክ ገመዶች ፋብሪካ በአማራ ክልል ዋና ከተማ ባህርዳር አካባቢ መሆኑ በራሱ የሚያሳየው ነገር አለ የሚሉት ባለሙያው የአባይ መነሻ የሆነውን የጣናን ውሀ መጠን ለመቆጣጠር ሆን ብለው ሰላዮቻቸውን በፋብሪካው ለመቅጠር አስበው እንደሆነ ተናግረዋል። የአሁኑን የግብጽ ድርጊት ቀድሞ በደርግ ጊዜ በፓዊ አካባቢ ይሰራ ከነበረው የጣና በለስ ፕሮጀክት ድርጊት ጋር አዛምደው የተናገሩት ባለሙያው፣ ያን ጊዜ ግብጾች ያካባቢውን አፈር በሰላዮች አማካኝነት ወደ አገራቸው እየወሰዱ በላብራቶሪ ይመረምሩና ፕሮጀክቱ የሚያሳድረውን ተጽኖ ለማወቅ ጥረት ያደርጉ ነበር ብለዋል። አሁን በባህርዳር ከተማ የሚያቋቁሙት ፋብሪካም ዋና አላመው ስለላ ማካሄድ መሆኑን አስረድተዋል።

የወያኔ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣የአገራችንን ጥቅም የሚያስከብር ስራ ከመስራት ይልቅ የአገራችንን ክብር የሚያዋርድ የክህደት ስራ በመስራት ላይ መገኘቱን ግንቦት7 በጥብቅ ማውገዙ ይታወሳል።

ሃይለ ሀሳብ
የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 88 ጥር 13 2002 ዓ.ም፤ ገጽ.3

# የሕዝብ ኑሮ፡ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና በኢትዮጵያ መሬት ላይ (ክፍል 1 ከፍስሐ ዘማርያም)

## እንደ መግቢያ

በፅንሰ ሀሳብም ሆነ በተግባር እንደሚታወቀው፤ ድህነት ትርጉምና መገለቻጫው ሰፊ ነው:: ድህነት መሠረታዊ ፍላጎቶችን መነፈግ፤ ማጣት፤ ማሟላት አለመቻል ነው:: ድህነት ረሀብና እርዛት ነው፤ በቂ መጠለያ አለማግኘት ወይም መጠለያ አልባ መሆን ነው:: ድህነት ንጹህ የመጠጥ ውሃ አለማግኘት ነው። መሠረታዊ ንጽህና በጎደለው ሁኔታና ከባቢ ውስጥ ለመኖር መገደድ ነው:: ጨቅላ ህፃናትና እናቶችን ጨምሮ ለቀላል በሽታዎች ሳይቀር በቀላሉ መጋለጥና ታሞ ለመታከም አቅም ማጣት ነው:: ድህነት ማንበብና መጻፍ አለመቻል ነው፤ ትምህርት ቤት የመሄድ ዕድል መነፈግ ነው፤ ትምህርት ቤት ገብቶም ጥራት ያለውና ለቁምነገር የሚያበቃ ትምህርት አለማግኘት ነው:: ድህነት ሥራ ማጣት ነው፤ ዛሬን ብቻ እንደ ምንም ማለፍ፤ ነገ ምግብ እንኳን ስለማግኘታችን እርግጠኛ አለመሆን፤ በፍጹም ፍርሐትና ስጋት መዋጥ፤ ተስፋ ማጣትና በሰቀቀን መኖር ነው:: ይህ ፍጹም ድህነት ነው:: ይህ 50 በመቶ የሚጠጋው የሐገራችን ሕዝብ የዕለት ተለት ዕጣ ፈንታ ነው:: በኢትዮጵያ ትልልቅና ትንንሽ ከተሞችም ያለው ረሃብና ዘግናኝ የኑሮ ውድነት እንደ ገጠሩ በግልጽ አይታይ ይሆናል:: ገና በዝርዝር ባለመዘገቡም ሊሆን ይችላል:: ያም ሆነ ይህ በኢትዮጵያ ከተሞች በኑሮ ውድነትና በድህነት የሚማቅቀው የመካከለኛውና የታችኛው መደብ ሕብረተሰብ ቁጥሩ በሚሊዮኖች የሚገለጽ ነው::

## የጽሁፉ ዓላማ

የዚህ ጽሁፍ (ክፍል አንድ እና ክፍል ሁለት) ዋና ጉዳይ የአብዛኛውን የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ የመሬት ላይ "የሲዖል" ኑሮና የቴሌቪዥን ላይ "የገነት" ኑሮ በንጽጽር ማየት ነው:: ንጽጽሩ የፕሮፓጋንዳውን ዓይን ማውጣትና ጎን ለጎንም የሕዝቡን የኑሮ ችግር ጥልቀት እንዲሁም አንገብጋቢነቱን በይበልጥ ለመገንዘብ ይጠቅም ይሆናል:: ኑሮአቸው በእጅጉ ተሻሻለ የተባሉ ጥቂት ሰዎች እንዲሁም የቁጥር መስፈሪያ የማያውቃቸውና በመሬት ላይ የማናያቸው መናፍስትም በኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና ሬዲዮ ነጋ ጠባ
ይቀርቡልናል:: በዚህ ክፍል የፕሮፓጋንዳው ባህርይ፤ ተልዕኮ፤ ዓላማ፤ ይዘትና አቀራረብ ይዳሰሳል:: በክፍል ሁለት ደግሞ በኢቴቪ ከሚቀርብልን የምናባዊ ፍጡራን የድሎትና የምቾት ኑሮ በተቃራኒው ያለውን ዕውነታ እናያለን:: ስለራሳችን ስለተራ ሰዎች ማለትም ሥጋና ነፍስ ስላለን ግለሰቦች፤ ስለቤተሰቦቻችን፤ ስለጎረቤቶቻችን፤ ስለሥራ ባልደረቦቻችንና ስለ ወገኖቻችን በመሬት ላይ የሚታየውን የዕለት ተለት ኑሮ፤ ቦታ፤ ጊዜና ሁኔታዎችን ያጣቀስን እኛው ራሳችን እንናገራለን - እንነጋገራለን::

የቴሌቪዥንና የመሬት ላይ ኑሮአችን ንጽጽሩ ጭማቂ ውጤት ቁጭትና ቁጣን ካጠናከረ አንድ ተፈላጊ ነገር ነው:: ማንና ምንድን ነው ለዚህ የዳረገን? ለመሆኑ ይህ ሐገርና በሥራ ላይ ያለው ፖሊሲ (መንግሥት) የማን ነው? የኛና የወገኖቻችንስ ነገር እንዴት ሊሆን ነው? ወደ ምን የባሰ አዘቅት ውስጥ እየወረድን ነው? ይህንን የአዘቅት ጉዞ እንዴት ነው የምንገታው? ከአዘቅቱ የምንወጣውስ በምን መላ ነው? ነገ ሳይሆን ዛሬና አሁኑኑ ምንና እንዴት ማድረግ አለብን? አጣዳፊ የለውጥ እንቅስቃሴን የሚሹ የህልውና ጥያቄዎች ናቸው::

በአጠቃላይ የዚህ ጽሁፍ ዓላማ፤ የሚያነበውን ሰው አፍታ ወስዶ በነዚህ ጥያቄዎች ዙሪያ የምር እንዲያንሰላስል መጎትጎት ነው:: እንደ ችግሩ ክፋት ከሆነና እንደ ባለጉዳይም፤ "ዕውነት የኛና የወገኖቻችን ኑሮና የሐገራችን ነገር እንዴት የሆነ ነው?" የሚለውን ጥያቄ ማንሳት ያለብን ገና ዛሬ ሳይሆን ትናንትና ከትናንት በስቲያ መሆን ነበረበት። ይህን ከአብዛኞቻችን ቀድመው ያደረጉና በማድረግም ላይ ያሉ ብዙ የለውጥ ፋና ወጊዎችና ተከታዮቻቸውም በሥራ ላይ መሆናቸውን ስለምናውቅ ከምሥጋና ጋር ጥሩ ስሜት ይሰማናል - ባለውለታዎቻችን ናቸውና። ሌሎቻችን ዛሬም ገና አልደነገጥን (ብርድም ሙቀትም የማይሰማን) ከሆነ ግን በቅድሚያ መፍትሔ የሚፈልግ ሌላ ትልቅ ችግር አለብን ማለት ነው። የለውጡን እንቅስቃሴ በአንድ ወይም በሌላ መልክ ለመቀላቀልና የበኩላችንን ለማገዝ ገና አልተዘጋጀንም ማለት ነው:: ይህ የኛ የብቻችን ችግር ሳይሆን የለውጥ መሪዎችም የቤት ሥራ ሊሆን ነው:: ፖለቲካዊ ማህበራዊና የኢኮኖሚ ፍትሕን ለማስፈን የሚደረግ የለውጥ እንቅስቃሴ የጥቂቶች ብቻ ትርዒት ሊሆን አይችልም:: ጥቂቶች መሪዎችም ብዙሃኑን ሕዝብ በተሻለ ሁኔታ የሚያንቀሳቅሱበትን የሚሰራ ሥልት ለመቀየስ ይችሉ ዘንድ መሬት ላይ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ በሚመለከት ያላቸውን መረጃ ወቅታዊ ማድረግ ይኖርባቸዋል:: ዞሮ ዞሮ ይህ ጽሁፍ የለውጥ መሪዎችም፤ ንቁ ተሳታፊና ደጋፊዎችም ሆኑ የዳር ቆሞ ታዛቢ ኢትዮጵያውያንም እንደየልዩ ሁኔታቸው እንዲያጤኑት የታሰበ ነው።

### የህዝብ ኑሮ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ላይ - በነርሱ ዓይን!

### "ሥራ ፈጣሪዎች"፤ "የምርት ጀግኖች" ና "ሚሊዮኔሮች"

ኢሕአዴግ በቴሌቪዥኑና በሬዲዮኑ የሚያሳየንና የሚነግረን የኢኮኖሚው ፖሊሲ በፈጠረላቸው ምቹ ሁኔታ ተጠቅመው ሚሊዮኔር የሆኑ በርካታ ተሸላሚ ገበሬዎች (የምርት ጀግኖች) ማፍራቱን ነው። አዲስ ያፈሩት ሐብትና ንብረት በቴሌቪዥኑ መስኮት እንድንቆጥረው ተደርድሮ ይቀርብልናል። አይሱዙው፤ ጎተራዎቹ፤ መጋዘኖቹ፤ የከብት መንጋው፤ ሰፋፊ የፍራፍሬና የጓሮ አትክልት ማሳዎቹ፤ የመስኖው እርሻ፤ የብረታብረትና የእንጨት ሥራ ድርጅቱ - ምኑ ቅጡ። የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ፖሊሲአቸውን ተከትሎ የተደራጀ፤ ቁጥሩ ከፍ ያለ ሕዝብ ከነበረበት ዝቅተኛው መደብ ወደ መካከለኛ መደብ መሸጋገሩን - ማደጉንም ያሳዩናል። እነዚህ የሚያቀርቧቸው ሰዎች መንግሥት የሰጣቸውን የብድር አገልግሎት...፤ ተጠቅመው የራሣቸውን ሥራ ፈጥረዋል፤ ለሌሎችም የሥራ ዕድል ፈጥረዋል እንባላለን። እናም እስካሁን በሕይወታቸው ቆጥረው የማያውቁትን የራሳቸውን ገንዘብ ለመቁጠር ችለው ኑሮአቸው ተለውጧል። "የአንጸባራቂው" ስኬታቸው ዝርዝሩ ረዥም ቢሆን አይገርምም ማለት ነው። ቤተሰባቸውን መደገፍ፤ ልጆቻቸውንም በጥሩ ትምህርት ቤት ከፍለው ማስተማር ጀምረዋል፤ በባንክ ተቀማጭ ገንዘብ መያዝ መጀመራቸውንም በኩራት ይገልጻሉ። ለራሳቸውና ለቤተሰባቸው ያማራቸውን መግዛት፤ መብላት፤ መጠጣት፤ ጀምረዋል:: የቤት ዕቃዎቻቸውን አሟልተው የተንፈላሰሱ በተድላና በደስታ ይኖራሉ (ኖሩ) ይባ..አ..ላ..አ..ል። ግሩም ተረት

### ሰዎቹ ምንድን ነው የሚፈልጉት?

የፕሮፓጋንዳው ዓላማ ግልጽ ነው። ከሰሜን፤ ከደቡብ፤ ከምሥራቅ፤ ከምዕራብ ኢትዮጵያ የአንድና የሁለት ወጣት፤ ወይም ሴት ወይም ገበሬ ወይም ባለሐብት ስኬት በተደጋጋሚና በማጋነን ያሳያሉ። ይህም ቢሆን ዕውነትና ውሸት ተቀላቅለው የሚቀርቡበት ነው። ዋናው ፍላጎታቸውና ጥረታቸው የጥቂቶችን የስኬት ታሪክ፤ የመላ ሐገሪቱ ወጣቶች፤ ሴቶች፤ ገበሬዎችና ባለሐብቶች የስኬት ታሪክ አድርገን እንድንወስድላቸው ነው። የነርሱን የማያባራ ፕሮፓጋንዳ ደጋግመን ስናይ፤ እኔ ብቻ እሆን እንዴ ወደ ኋላ የቀረሁት? ሌላው ሕዝብ - ሐገሩ አልፎለታል ማለት ነው? ብለን እራሳችንን እንድንጠራጠርና ጥፋቱ ያለው እነሱ ጋ ሳይሆን እኛ ጋ ሳይሆን አይቀርም እንድንል ነው የሚፈልጉት። ስለ አስከፊው የዕለት ኑሮአችን በአዕምሮና ልባችን የተቀረጸውን ትክክለኛ ግንዛቤ፤ እምነት፤ ንዴትና ቁጭት ከቦታው ማጥፋት ነው ዋናው ፍላጎታቸው። በምትኩም ውሸትን ደጋግሞ በማሳየት አእምሮአችንን ማጠብና የሌለውን አለ፤ ያለውን የለም ብለን ለእነርሱ የሚመች የተሳሳተ ግንዛቤ፤ እምነትና አድናቆት እንድናዳብር ነው የሚፈልጉት። በተጨባጭ ሥራ ሳይሆን በሐሰተኛ ወሬያቸው ብዛት ስለነርሱ ያለንን አመለካከት እንድንቀይር፤ በዙሪያቸው በደጋፊነት እንድንኮለኮልና ከኢሕአዴግ ወዲያ ድርጅትና መንግሥት ለአሳር እንድንል ይፈልጋሉ። የ "ሺህ ዓመት ያንግሥልን" መፈክሩም አትረሣም፤ የፕሮፓጋንዳቸው አዝማች ነች። የኑሮ በቴሌቪዥን ዋናው ጉዳይ ውዳሴ ኢሕአዴግ ካልሆነ ሌላ ታዲያ ምን ሊሆን ነበር? ከንቱ ልፋት! የቴሌቪዥን ፕሮፓጋንዳ ሌላ የመሬት ላይ ዕውነታው ሌላ። በጣም የሚያናድደው ለተመልካችና አድማጭ ያላቸው ንቀትና ዝቅተኛ ግምት ነው። ሕዝቡን ያውም የራሱን የዕለት በለት የኑሮ ዕውነታ ለማስተዋል፤ ለማሰላሰል፤ ለማገናዘብ፤ ለመረዳት፤ ለመመዘንና ፍርድ ለመስጠት አቅም የለውም ብለው ያምናሉ። ይህ ለሕዝብ ስድብ ነው!!

### ተውኔቱ፤ ደራሲ፤ አዘጋጅና ተዋናዮቹ

ወደጀመርነው ነገር እንመለስና፤ ከላይ ተሸለመ የተባለው ገበሬ (የምርት ጀግና) ዓይነት ዘመድ ወዳጅ ያላችሁ ሰዎች ሁኔታውን በሚስጥር ጠይቁት። የሚያምናችሁ ከሆነ በቴሌቭዥን የተፈጸመውን ማጭበርበርና ዕውነተኛውን የእርሱን ታሪክ ጎን ለጎን አድርጎ ያሳያችኋል። (በቴሌቪዥን ቀርቤ አልዋሽም ብሎ የሚያንገራግርም ድንገት ከተገኘ ሰበብ ተፈልጎ ይታሰራል። ይህ የተደረገና የሚደረግም ነው።) በቴሌቪዥን ከተናገረው ቃልና በማስረጃነት ካሳየው ሐብት ውስጥ ሰባ አምስት በመቶ የሚሆነው በቤቱና በእጁ የሌለ ከበላይ አካል ተቀናብሮ የተሰጠው ሐሰተኛ የፈጠራ ሐብት ብቻ መሆኑን ይነግራችኋል።"ከበላይ አካል" ያልኩት የተውኔቱ ደራሲዎች (የፕሮፓጋንዳው ነዳፊዎች) ከጫካ ባመጡትና ከደርግም በወሰዱት ድርጅታዊ የአሠራር ዘዴ የተቀነባበረ ፕሮግራም መሆኑን ለመጠቆም ነው። ተዋናዮቹም ("የምርት ጀግኖቹ") ሙሉ በሙሉ በጥንቃቄ የተመረጡ የኢሕአዴግ ካድሬ፤ አባልና ወይም ደጋፊ ናቸው። የፕሮፓጋንዳው ፕሮግራም በሚሰራበት አካባቢ ያለው የኢሕአዴግ (የመንግሥት) መዋቅር ሰዎች ናቸው የሚጠየቁትን ሰዎች መርጠውና አስጠንተው ለኢቴቪና ሬዲዮ "ጋዜጠኞች" የሚያስረክቡት። ከላይ ከተገለጸው አንዱም ተራም ሆነ ጠንቃቃ ግምት ወይም ጭፍን ክስ አይደለም። በዓይናችን ያየነው በጆሮአችን (አንዳንዴም ከራሳቸው) የሰማነው ነገር ነው። የኢሕአዴግ መዋቅር እኮ 'ወንፊት' ነው። ምሥክር መቁጠሩ ይጠቅማልና ነው እንጂ፤ የሚፈጸመውን ማጭበርበርማ ኢቴቪን ወይም ሬዲዮ የተከታተለ ኢትዮጵያዊ ሁሉ በየዕለቱ የሚታዘበው ነገር ነው።

የኛ ምሥክርነት ይቆይ። በሣምንታዊው 'አዲስ አድማስ' ጋዜጣ ላይ (ታህሣሥ 17/2002 ዓ.ም.) "***ከዚህ ውጭ ምን ማደረግ እንችላለን?***" በሚል የተማጽኖ ጥያቄ (ንዑስ ርዕስ) አንድ የኢቴቪ ባልደረባ የተናዘዘውን ተመልከቱ። "ኢቴቪ ... (በራሱ) አቅዶ የሚሰራቸው ፕሮግራሞችና ዜናዎች እጅግ ጥቂት ናቸው። ፖሊቲካዊ ይዘት ያላቸው ፕሮግራሞች ዕቅድ ይዘት የሚወሰነው ከድርጅቱ ውጭ (በመዋቅር) ባሉ የመንግሥት ባለሥልጣናት ነው።" ብሏል የኢቴቪው ባልደረባ (እግዜር ያውጣውና።) ይኸው ውስጥ አዋቂ በተጨማሪም ጣቢያው በቅርቡ በግል ጋዜጦች ላይ አስጸያፊ የስም ማጥፋት ዘመቻ ያካሄደበት ፕሮግራም ስለተዘጋጀበት ሁኔታ የምሥክርነት ቃሉን ሰጥቷል። ይህም አጠቃላዩን የኢቴቪን አሠራር ቁልጭ አድርጎ ያሣያል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

# ሃይለ ሀሳብ

## የሕዝብ ኑሮ፡ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና. . . (ከገጽ 3 የቀጠለ)

“ዕቅዱ የመጣው ከድርጅቱ ውጭ ባሉ የመንግሥት የሥራ ሃላፊዎች ነው። በፕሮግራሙ ላይ የሚጠየቁ ሰዎች፤ የስክሪፕቱ አጻጻፍ፤ ይዘት፤ አቀራረብ ተወስነ፤ ሌላው ቀርቶ በሚስጥር እነማን እንደሚያዘጋጁ (ከጥቂቶቹ በስተቀር የገዢው ፓርቲ አባላት ናቸው)፤ ስክሪፕቱ ሲጻፍ፤ ምስል ሲቀናበር የላይኞቹ ሲያዩት፤ ይሄ ይጨመር ይሄ ይቅር ሲሉ ቆዩ በመጨረሻ የበላይ ሃላፊዎቹ ሲፈቅዱ ተላለፈ:: ” ዕውነታው ይህ ነው።

በነገራችን ላይ ፕሮግራም በሚስጥር እንዲያዘጋጁ የሚመረጡት ሰዎች ኢሕዴጋዊ መጠሪያቸው ”ልማታዊ ጋዜጠኞች“ አይደል? እነዚህ የአዲስ ነገሩ ጋዜጠኛ “ዞምቢዎቹ” የሚላቸው ዓይነት ናቸው:: ዞምቢዎች!! እነዚህ ዞምቢዎችና ጌቶቻቸው የበሬ ወለደ ቅጥፈትና ፕሮፓጋንዳቸውን በቀላሉና በማንአብኝነት ለማሰራጨት የማይቸገሩበት ምክንያት ግልጽ ነው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት፤ የሐገሪቱ ሰፊ የቆዳ ስፋት፤ የተራራቀ የሕዝብ አሠፋፈር፤ የመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ አለመስፋፋትና የነጻ ሚዲያ ክልከላና አፈናው አንድ ላይ ሆነው ነው የተመቿቸው።

በዚህ መሥመር እንዲቀጥሉ የሚገፋቸው ሌላው ነገር ደግሞ ስለ ፕሮፓጋንዳ ምንነት ያላቸው የተሳሳተ ናእውቀትን እና ናተሞክሮ ነው። ”አንተ ብቻ ሳትታክት ውሸትን ተናገር፤ ከመደጋገም ብዛት ዕውነት መስሎታይ ይልሀል።“ የሚለውን መመሪያ ከየትኛው አምባገነን እንደተማሩት እናውቃለን። የኢትዮጵያ ሕዝብ በምርጫ 97 ዋዜማ ለአጭር ጊዜ የውስጡን ሀሳብ የመግለጽና መረጃ የመለዋወጥ ነጻነት አግኝቶ ነበር። ያንን በሚገባ ተጠቅሞ ስለኢሕአዴግም ሆነ ስለ አደንቋሪ ፕሮፓጋንዳው ያለውን ጥልቅ ግንዛቤና መከፋትና መቆጣቱንም አሳይቷል። ጽኑ የሆነ የለውጥ ፍላጎቱን በምርጫ ድምጹና ካርዱ በዓለም ፊት ገልጿል። ኢሕአዴግም ይህንን የሕዝብ ጠንካራ ዕውቀት፤ እምነትና አቋም ስለተረዳና ሕዝቡንም ስለፈራ ይመስላል ፕሮፓንዳውን እንዲያውም ይበልጥ አጠናክሮ የቀጠለበት። መረዳቱስ ባልከፋ ነበር። ግምገማውና የሄደበት የእርምት አቅጣጫ ግን እጅግ የተሳሳተ ነው። “ሕዝቡ የጠላን ስላልሠራንለት ሳይሆን፤ የሰራንለትን በቅጡ ስላልነገርነው ነው። ስለዚህ መፍትሔውና የቀረን ነገር ሚዲያውን ሁሉ የልማታችን አብሳሪ ማድረግ ብቻ ነው። በውስጡ ያሉትንም ተቀጣሪዎች ልማታዊ ጋዜጠኛ ብሎ የውሎአችንን ዜና አቀናባሪና የገድላችን አብሳሪ ማድረግ ብቻ ነው፤ በቃ።” ’ራዕይ’ የሚባለውን የርእዮተ ዓለም መጽሔታቸውን ተመልከቱ። ሌላ ግምገማና መፍትሔ የለም። ስለዚህ ኢሕአዴግ ከቴሌቪዥን መስኮት ላይወርድ ምሏል። ይሄ የሚሆነው ከሥልጣን ሲወርድ ብቻ ነው። እርማችሁን አውጡ! እርሱ እንደሆነ “ዲሽ የሌላችሁ እንዴት አመሻችሁ!’ እያለን ይቀጥላል። እናም በመሬት ላይ ያለውን አስቀያሚ ገጽታውን ለማሻሻል ከመጣር ይልቅ በቴሌ ቪዥን ላይ ተጣብቆ በበሬ ወለደ ቅጥፈት መዋል ማደሩን መርጧል።

**(ክፍል 2 በሚቀጥለው ሳምንት ይቀጥላል)**

## ወያኔ በጥምቀት በአል አከባበር . . . ከገጽ 1 የዞረ

ወያኔ በነባር ወታደሮቹ ላይ ያለው እምነትም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሸረሸረ በመምጣቱ፣ በተለይ የአማራና የኦሮሚያ ተወላጅ የሆኑ የሰራዊት አባላትን በአዳዲስ አባላት ለመተካት ዝግጅቱን እያጠናቀቀ እንደሚገኝ ከመከላከያ ምንጮቻችን የደረሰን መረጃ አመልክቷል።

የቱንም ያክል ሰራዊት ቢያዘጋጅ ወያኔ ከውድቀት አይድንም የሚሉት አስተያየት ሰጪዎች፣ ሀይላቸውን በወታደሮች ላይ ያሳረፉ ገዢዎች ለውድቀታቸው መንስኤ የሚሆኑት ራሳቸው የሚተማመኑባቸው የሰራዊት አባላት ይሆናሉ ሲሉ በመንግስቱና በሀይለስላሴ ዘመን የነበረውን ታሪክ በመጥቀስ አስረድተዋል ። በሰራዊቱ ውስጥ የሚታየው የዘር ክፍፍል፣ የትግራይ ተወላጅ የሆኑ የሰራዊቱ አባላት ቁልፍ የአዛዥነት ቦታዎችን መያዛቸው እንዲሁም አብዛኛው ሰራዊት ቤተሰቡን ለማስተዳደር ተስኖት እያለ ጥቂት የሰራዊቱ አዛዦች በርካታ ሚሊዮኖችን የሚያወጡ ቤቶችን በመገንባት ላይ መሆናቸው፣ ወያኔ በገዛ የሰራዊቱ አባላት የሚበላ ለመሆኑ አመላካች ናቸው የሚሉ አስተያየቶችም ለዝግጅታችን ክፍላችን ደርሰዋል። ሰራዊቱ ተወጥሮ በተያዘበት የስለላ ስራ ምክንያት በአንድነት ይነሳል ተብሎ ባይጠበቅም፣ ተቃዋሚ ሀይሎች በወያኔ ላይ የተጠናከረ እርምጃ መውሰድ በሚጀምሩበት ጊዜ ግን ሰራዊቱ እየሸሸ የተቃዋሚውን ጎራ በመቀላቀል የወያኔን ሞት ያፋጥነዋል ሲሉ አስተያየታቸውን ያጠናክራሉ።

## ኢትዮጵያውያን ለዲሞክራሲ የሚያደርጉት . . . ከገጽ 1 የዞረ

“ምንም አይነት ተመሳሳይ የሆነ እሴት ከሌለው አገዛዝ ጋር ምእራባዊያን መንግስታት ጠንካራና ቋሚ ግንኙነት መመስረት አይችሉም” የሚሉት ዶ/ ር ብርሀኑ በተለይ የአሜሪካውያን እሴቶችና ጨዋነት መሰረቱ ነጻነትን ከመውደድ የመጣ በመሆኑ፣ አሜሪካውያን ይህ እሴታቸው በመላው አለም እንዲሰራጭላቸው የሚፈልጉ መሆናቸውን እንደሚያምኑና ወያኔ ግን ይህን እሴታቸው በኢትዮጵያ እንዳይሰርጽ እንቅፋት እንደሆነ ገልጸዋል። ጋዜጠኛው ዶ/ር ብርሀኑ ከንቲባ ሆነው መመረጣቸውን፣ እስረቤት መግባታቸውንና የቅንጅት አመራር በነበሩበት ጊዜ በአገራቸው ዲሞክራሲን ለማምጣት ሲያደርጉ የነበሩትን ጥረት አስታውሶ ዘግቧል።

## የወያኔ የግድያ ሀይሎች እርስበርሳቸው . . . ከገጽ 1 የዞረ

አቶ ሙሉነህ ድርጊቱን ከመጪው ምርጫ ጋር አያያዘው ሲናገሩ፣ “አገዛዙ ስልጣኑን ለማቆየት ሀይልን እንደብቸኛ አማራጭ መውሰዱ በምርጫው ለመሳተፍ ላቆበቆቡት የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ትልቅ ትምህርት የሚሰጥ ነው፣ ምክንያቱም ወያኔ ስልጣኑን ለማቆየት ማንኛውንም ሀይል ከመጠቀም ወደ ሁዋላ እነደማይል ዛሬም እየታየ ነው፤ ይህ ከሆነ ደግሞ በካርድ ስልጣን ይለቃል ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው።” ብለዋል።

መጪው ምርጫ ዴሞክራሲያዊና ፍትሀዊ እንዲሆን ካስፈለገ የ97 ምርጫ ሂደት ሂሳብ መወራረድ አለበት የሚሉት አቶ ሙሉነህ፣ ያ እስካልሆነ ድረስ ስለምርጫ ማውራት ጉንጭን ከማልፋት ውጭ ሌላ ጥቅም የለውም ብለዋል። የግንቦት97 ሂሳቦች ምንድን ናቸው ለተባሉት ሲነገሩ ደግሞ “ በመጀመሪያ ወያኔ ህጋዊ መንግሰት አይደለም፣ ህዝብ አልመረጠውም፣ መፈንቅለ ህዝብ አድርጎ ስልጣን የያዘ ቡድን ነው። ስለዚህ መፈንቅለ ህዝብ ማድረግ ስህተት መሆኑን አምኖ መቀበልና ስልጣኑን ለባላደራ መንግስት ማስረከብ አለበት። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የህዝብን ስልጣን መቀማት ብቻ ሳይሆን የስልጣን ባለቤት የሆነውን ህዝብም ጨፍጭፏል። ለዚህም ሀላፊነት መውሰድ አለበት። በተጨማሪም ከምርጫ 97 ወዲህ መንግሥት አልባ የሆነቺውን ጎረቤት አገር ሱማሌን በመውረር በፈጸመው የጦር ወንጀል በሁለቱ ህዝቦች መካከል ለዘመናት የማይሽር ቂም ፈጥሮአል ፤ በኦጋዴን ወገኖቻችን ላይም በአለም አቀፍ ደረጃ እየተወገዘ ያለ ሰብ ዓዊ ሰቆቃ እየፈጸመ ነው ፤ የአገራችንን ለም መሬት ለባዕዳን በሽያጭ እየቸበቸበ ነው፤ ከጎረቤት ሱዳን የሚያዋስነውን ከ1600 ኪሎ ሜትር በላይ ርዝመት ያለውን መሬትም አሳልፎ ለሱዳን በመስጠት የአገር ክህደት ወንጀሉን አጠናክሮ ቀጥሎበታል፤ የፖለቲካ ተቀናቃኞችን የማሰር፤የመግደልና የማፈናቀል ተግባር አልተገታም ወዘተ እና ለመሳሰሉት ሁሉ ሃላፊነት በመውሰድ እዳዎቹ በቅድሚያ መወራረድ ይኖርባቸዋል” ሲሉ ገልጸዋል። ከእነዚህ በተጨማሪም ይላሉ አቶ ሙሉነህ “ አገዛዙ እንደዚህ አይነት አሳፋሪ ድርጊቶች እንዳይደገሙ ለማድረግ ተቋማዊ ለውጦችን ማድረግ ይጠበቅበታል። የፍትህ፣ የጸጥታ፣ የመከላከያ፣ የምርጫ ቦርድ ፣ የመገናኛ ብዙሀን ና ሌሎችም መንግስታዊ ተቋሞች ዜጎችን በእኩል ለማስተናገድ በሚችሉበት ሁኔታ እንደገና መዋቀር አለባቸው። እነዚህ መዋቅራዊ ለውጦች ከልብ ሲተገበሩ ያን ጊዜ ሁሉም ተማምኖ ወደ ምርጫ መግባት ይችላል።” ሲሉ አስረድተዋል።

የኢትዮጵያ ህዝብ ከዚህ ምርጫ ምን ይጠብቃል ለተባሉት አቶ ሙሉነህ ሲናገሩ “የኢትዮጵያ ህዝብ በወያኔ ዘመን ፍትሀዊና ዲሞክራሲያዊ ምርጫ እንደማይኖር በ97 ምርጫ ወቅት አይቶታል። ስሜቴን በምርጫ እገልጻለሁ ብሎ ተገድሎአል፣ ታስሮአል፣ ተገርፏል ወይም ተሰዷል። ያንን መስዋትነት እንደገና ለመክፈል የሚያስችሉትን ሁኔታዎች እየተመለከተ አይደለም። አሁን የሚታየው እውነታ ህዝቡ ምርጫ ለሚባለው ነገር ቁብ ያልሰጠው መሆኑን ነው። ህዝቡ አሁን እያለ ያለው ወያኔ በየትኛውም መንገድ ተወገዶ እንየው ነው። ስለዚህ ህዝቡ ከምርጫው ምንም የሚጠብቀው ነገር የለውም። የሚጠብቀው ከምርጫ ሳጥን ሳይን ከሀይል ሳጥን ነው። ብለዋል።

ግንቦት7 በዚህ በኩል ምን እንቅስቃሴ እያደረገ ነው ለተባሉት ሲመልሱም “ ግንቦት7 ከኢትዮጵያ ህዝብ ስሜትና እምነት ጋር ተመሳሳይ የሆነ ስሜትና እምነት አለው።ግንቦት7ትም ሆነ ህዝቡ በወያኔ ዘመን በምርጫ ካርድ የመንግስት ለውጥ ይመጣል ብሎ አያምንም። ህዝቡም ሆነ ግንቦት ሰባት ወያኔ በየትኛውም መንገድ መወገድ አለበት ብለው ያምናሉ። አሁን ግንቦት7 እየሰራ ያለው ይህን የህዝብ ጥሪ እውን ማድረግ ነው። ወያኔን የተለያዩ አማራጮችን ተጠቅሞ ከስልጣን ማባረር ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ነው ብሎ በከፍተኛ ሁኔታ እየተንቀሳቀሰ ነው። ከህዝቡ ጋር በመሆንም ለድል ይበቃል።” ሲሉ አጠቃለዋል።

በተያያዘ ዜናም ህዝቡ የተቃዋሚ ድረጅቶች አመራሮችን የህይወት ዋስትና እና የምርጫ ዋስትና እንዲሰጧቸው በመጠየቅ ላይ ነው። የተቃዋሚ አባላት በአንዳንድ የገጠር ቦታዎች ህዝቡን ሄደው ለማናገር ሲሞክሩ ከህዝቡ የሚቀርብላቸው ጥያቄዎች ግን ለመመለስ አስቸጋሪዎች ናቸው ተብሎአል። በአንድ አካባቢዎች ህዝቡ ለምርጫ ቀስቃሾች “ ዘንድሮም ለህይወታችንና ለድምጻችን መከበር ዋስትና የሚሰጠው ወያኔ ነው።ወያኔ ደግሞ በ97 ምርጫ ወቅት የሰጠንን ዋስትና ከዶ ልጆቻችንን ፈጅቷል ድምጻችንንም ሰርቋል።ስለዚህ ከወያኔ የሚሰጠውን ዋስትና አምነን አንቀበልም። ሁለቴ መታለል ጅልነት ነው። እናንተ ለህይወታችንና ለድምጻችን ምን ዋስትና ትሰጡናላችሁ? ልጆቻችን ቢሞቱ የልጆቻችንን የደም ካሳ ትከፍላላችሁ? ድምጻችን ቢከበር ወያኔን በመሳሪያ ሀይል ተጠቅማችሁ ድምጻችንን ታስመልሳላችሁ? ይህንን እናደርገለን ብላችሁ ትፈርሙልናላችሁ?” የሚሉ ጥያቄዎችን እንዳቀረበ ያገኘነው መረጃ አመልክቷል።

## የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

**በ 7530 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 9610 KHZ በ 31 ሜትር ባንድ** ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

## ውድ አንባቢዎቻችን

ለፕሮግራሞቻችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን g7radio@ginbot7.org ወይም በስልክ ቁጥር 0044- 203-286- 9661